# የሐረሪ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት(ሐዲድ)

# የሐሪሪ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ አንድነት የህዝብ ንቅናቄ (አጭር ማኒፌስቶ)

## I. መግቢያ

በአገራችን ኢትዮጵያ ለዘመናት ተጭኖት የነበረው ጭቆና በተደረገው መራር ትግል ተወግዶ በምትኩ የብሔር ብሔረሰቦችና የህዝቦች እና የዜጎችን መብቶች ህገመንግስታዊ እውቅና አግኝቶ ክልሎች ራሳቸውን በራሳቸው በማስተዳደር ላይ ይገኛሉ ። በኢፌድሪ ህገመንግስት በተደነገገው መሰረት ከተዋቀሩት የክልሎች አንዱ የሐረሪ ህዝብ ክልል ነው ።

የሐረሪ ህዝብ ክልል የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ መብት የሚከበርበትና በክልሉ የሚኖሩ ብሔር ብሔረሰቦች ጋር በሰላም በመቻቻል በጋራ የሚኖረበት በመሆኑ የክልሉ ህገመንግስት መሰረት በማድረግ ክልላዊ መንግስቱ ከተዋቀረ ከ15 አመታት በላይ ይሆናል ።

ሆኖም የሐረሪ ህዝብ በህገመንግስት የተረጋገጠለትን ፓለቲካዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መብቶች በአግባቡ ተሳትፎና ተጠቃሚ እንዲሆን የተደረጉ ጥረቶች ቢኖሩም ህዝቡን በአግባቡ አደራጅቶ በማነቃቃት ተጠቃሚነቱን ሊያረጋግጥለት የሚችል ሀይል ባለማግኘቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚያሰማው እሮሮና ቅሬታ በመበረታቱ ለችግሩ መፍትሔ የሚሰጥ ተቋም በህዝቡ ተሳትፎ የህዝቡን የሰላምና የልማት የመልከም አስተዳደር ፍላጎት ለማርካት ይህን ንቅናቄ ማቀጣጠል አስፈላጊ ሆኗል ።

ስለዚህ በዚህ ፅሁፍ የሐረሪ ህዝብ ያለበትን ነባራዊ ሁኔታ ንቅናቄው ያስፈለገበት ምክንያት የንቅናቄው ራዕይ ተልዕኮና እሴት የንቅናቄው አለማዎችን የሚገልፅ ማኒፌስቶ በአጭሩ የተገለፀ ሲሆን ህዝቡ የንቅናቄው ባለቤት ሆኖ የንቅናቄው ተጠቃሚ እንዲሆን ጥሪያችንን እናስተላልፋለን ።

## II የሐረሪ ህዝብና ክልል ነባራዊ ሁኔታ

### ሀ) የሐረሪ ህዝብ የታሪክ አጠቃይላ ገፅታ

የሐረሪ ህዝብ በምስራቅ ኢትዮጵያ ለረዥም ዘመናት የቆየ በራሱ ቋንቋ የሚማርና የሚተዳደር ህዝብ ነበር ። ህዝቡ ራሱን የቻለ መንግስታዊ መዋቅሮች የነበሩትና 72 አሚሮች የነበሩት እንዲሁም የራሱ የሆነ የመገበያያ ገንዘብ የነበረው የራሱ የሆነ የፍ/ቤት መዋቅር (ዲዋን) የነበረውና የፍትህ አካላት ፓሊስ እና መ/ቤት ነበረው ። ህዝቡ ከአጎራቦች ህዝቦች ጋር የጠነከረ ትስስርና በፓለቲካ በማህበራዊና በኢኮኖሚ በጋራ ተሳስሮ ይኖር የነበረ ህዝብ ነው ። የኢኮኖሚ እንቅስቃሴውም በዋናነት ያግብርና ውጤት ( ቡና ጥጥ ፍራፍሬ )

እስከውጭ ድረስ ኤክስፐርት በማድረግ የአነስተኛና የእደጥበባት ውጤቶችና ወርቅና የባሪያ ንግድ በብዛት ይካሄድባት ነበር ባጠቃላይ ሐረር የምስራቅ ኢትዮጵያ የንግድ ማዕከል ነበረች ። በተጨማሪም ሐረሪ የስልምና ሀይማኖት ትምህርት ማስፋፊያ እና ማስራጫ ማዕከልም ነበረች ሐረሪ ልዑላዊነቷን በወራሪው የአፄ ሚነሊክ ጦር በሀይል እስኪነጠቀ ድረስ በምስራቅ ኢትዮጵያ ገናና ታሪክና ባህል ያላት መሆኑን መላው አለም የመሰከረው ሀቅ ነው።

ሆኖም የሀረሪ ህዝብና መስተዳደሩን ነፍጠኛው የሚኒሊክ ሰራዊት በጨለንቆ ጦር ሜዳ የአሚር አብዱላሂን ሰራዊት በሀይል በመንጠቁ መስተዳድሩ መዋቅር ፈርሷል ፣ ህዝቡ ተጨፍጭፏል፣ በቋንቋውና በታሪኩ መጠቀም መብቱን ተነፍጓል ፣ የሀይማኖት ተቋሟት ፈራርሰዋል ባጠቃላይ ህዝቡ መብቱ ተረግጦ የኢኮኖሚ መሠረቱ ተንዶ ማህበራዊ ዋስትናውን አጥቶ በጭቆና ቀንበር ስር ወደቀ ።

የሐረሪ ሕዝብ ከምኒሊክ እስከ ደርግ ውድቀት የተለያዩ ሰውርና ግልፅ ተፅኖዎች በማድረግ ነፃነቱና መብቱ ተረግጦ ቢቆይም በግልፅና በስውር የተለያዩ አመጾችና ተቃውሞዎች ሲያሰማ ቆይቷል የተካሄዱት የትግል እንቅስቃሴዎች የሐረሪ ህዝብን ህልውና ለማጥፋት የተካሄደውን ዘመቻ ለመቋቋም ያስቻለና አሁን ለተገኘው ነፃነት የበኩሉ አስተዋጽኦ እንዳለው ይታወቃ ።

# ለ) የኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች

የሐረሪ ህዝብ ባለፉት ስርአት እንደ ህዝብ የኢኮኖሚ መብቱ ተረግጦ የቆየ ህዝብ በመሆኑ በዚህ ስአት ሙሉ መብት ህገመንግስታዊ ዋስትና ቢያገኝም ። የመብቱ ተጠቃሚ ሲያደርጉ የሚያስችሉ አደረጃጀቶች አወቃቀሮችና አመራሮች ላይ ባለው ችግር ተሳታፊና ተጠቃሚ አልሆነም ። የክልሉ የኢንቨትመንት እንቅስቃሴ ደካማ መሆኑ የመሰረተ ልማት እንቅስቃሴ መዳከሙ ሕገወጥ ንግድና ግንባታ መስፋፋት ተክክለኛ የከተማ ልማት ፓሊሲ አሰፈጻሚ አመራር ብቃት በማነሱ የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ማስፋፋትና ማሳደግ አለመቻልና ከተማና የገጠር ትስስርና የማስተር ፕላን አለመመራት በዋናናት የሚጠቀሱ ናቸው።

# ሐ)የማህበራዊ ሁኔታ

የሐረሪ ህዝብና ክልል የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በተፈለገው መልኩ ባለማደጉ የማህበራዊ ችግሮች ከግዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ መጥቷል የማህበራዊ ተቋማት አቅርቦት አቅም በመድከሙና በማነሱ ህዝቡ ከክልሉ ወደ ሌላ ቦታ የመሰደድ የከተማ ስራ አጥነት አደገኛ ቦዘኔዎችንና ጎዳና ተዳዳሪነት HIV ኤድስ መበራከት የወንጀል መብዛት ባጠቃላይ ክልሉ ወደ ማህበራዊ ቀውስ በማምራት ላይ ይገኛል ። በክልሉ ቋንቋ የመሰራትና የመዳራጀት መብት ከወረቀት አላለፈም

## መ) ፖለቲካዊ ሁኔታ

የሐረሪ ህዝብ አሁን በተፈጠረው የዲሞክራሲ ስርአት በመጠቀም በፖለቲካ ፓርቲ የመደራጀት እንቅስቃሴ ነበረው የሐረሪ ብሔራዊ ሊግ ( ሐብሊ) በመመስረት በፓለቲካው ተሳትፎ ቢያደርግም በነበረው አለ መግባባት ሁለተኛ ተቀናቃኝ ፓርቲ የሐረሪ ህዝብ አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (ሐዲአፓ) ተመስርቷል ሆኖም በመሀል የነበረው ሽኩቻ ህብረተሰቡን ወደ ባሰ ቀውስ ያመራውና የነበረውን የፓለቲካ ስሜት በእጅጉ የጎዳው ነበር ። በተጨማሪም ለሶስት የምርጫ ዘመናት ገዢ ፓርቲ የነበረው ሐብሊ ህዝቡን አንድ አድርጎ በማስተባበርና ክልሉን በማልማት ከፍተኛ የአመራር ብቃት የጎደለውና ህዝቡን በመልካም አስተዳደር እጦት ያማረረ በመሆኑና ጥገኛ አመራርና ባለሀብት የተቆጣጠረው ፓርቲ በመሆኑ የህዝቡ እምነት በከፍተኛ ደረጃ ወድቋል።

# III የንቅናቄው ራዕይና ተልኮና እሴቶች

ሀ) <u>ንቅናቄው ያስፈለገበት ምክንያት</u> ፦ የህዝቦችን ህልውና የሚወስኑ ተግባራት በድል መወጣት የሚቻለው ምልአተ ህዝቡ በንቃት ሲሳተፉበት ነው። የህዝባችን ዋነኛው የኢኮኖሚ ሀብታችን በመሆኑ ህዝብ የሠላም የልማትና የመልካም አስተዳደርና የዲሞክራሲ ስርአት ግንባት ዋነኛና ትልቁ አቅም ነው ።አሁን ያለው የመንግስት መዋቅር በመልካም አስተዳደር እጦት እና በአመራር ብቃት ማነስ የህዝቡን ፍላጉት ያላሟላና ህዝቡን በአግባቡ የማያሳትፉና ተጠቃሚ የማያደርግ በመሆኑ የፓለቲካ ድርጅቶችም በህዝቡ ስም የመንግስት ስልጣናቸውን ከመያዝ ያለፈ ህዝቡን በአንድነት አደራጅቶ ለመምራት ባለመቻላቸው ህዝቡ አደጋ ላይ እንዳይወድቅና የህዝበ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ይህን ንቅናቄ በህዝብ ፍላጎት በህዝቡ ተሳትፎ ህዝቡን ተጠቃሚ የሚያደርግ አካል ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል ።

ለ) <u>የንቅናቄው ራዕይ</u>

የሐረሪ ህዝብ አንድነት ንቅናቄ ራዕይ የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ መብት ተከብሮ ክልላችንን የልማት እና የመልካም አስተዳደር ተምሳሌትና አውራ፣ ለነዋሪዋቿ ምቹ ሆና ማየት ነው።

ሐ) <u>ተልእኮ</u>

የሐረሪ ህዝብ በነቂስ በማሰተፍ ህዝቡን የፓለቲካ የማህበራዊና የኢኮኖሚ መብቶች ተጠቃሚ ማድረግ ነው።

መ) <u>እሴቶች</u>

የተበታተኑ ሐረሪዎችን በአንድነት በማሰባሰብ፣ህዝቡን አቅም በአግባቡ መጠቀም

ሀ) የመልካም አስተዳደር መርሆዎችን ማክበር

ለ) ታሪካዊና ባህላዊ እሴቶችን መጠቅና ለልማት ማዋል

ሐ) መልካም ስነምግባርና ታታሪነት ባህላችን ነው::

መ) ህገ መንግስቱንና ህገመንግስታዊ ስርአትን መጠበቅ

ሠ) ልማታዊና አብዬታዊ ዲሞክራሲያዊ መስመር ማክበር

## ሠ) የንቅናቄው አጠቃላይ ግቦች

የሐረሪ ህዝብ ገናና ታሪክና ባህል ያለው ለልማት ለመልካም አስተዳደርና ለዲሞክራሲ ስርአት ሙሉ በሙሉ ፅኑ የሆኑ አቋም ያለው ህዝብ ነው:: ህዝቡ በእውቀቱ በጉልበቱና በገንዘቡ ለክልሉና ለኢትዬጵያም ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማበርከት የሚችል ትልቅ አቅም ያለው ህዝብ ነው በዚህ እምቅ ሀብትና በክልላችን ያለው እምቅ የሀብት መረጃ በአግባቡ አደራጅተን በመጠቀም ለአገራችን ጥሩ ተምሳሌት ሊሆን የሚችል ስራ መስራት ይቻላል ::

በመሆኑም የሚከተሉትን አጠቃላይ ግቦች መሠረት በማድረግ የተለያዩ የንቅናቄ አጀንዳዎችን በመቅረጽ በአግባቡ በመምራት ህዝቡን ለማሳተፋና ተጠቃሚ ለማድረግ ነው::

1) የሐረሪ ህዝቡ ህገ መንግስታዊ መብቶች በማረጋገጥ ተስታፊና ተጠቃሚ ማድርግ
2) የሐረሪ ህዝብ ታሪክ ቋንቋ ና ባህልና ቅርሶች በአግባቡ በህብረተሰብ ተሳትፎ ተጠበቆ ለኢኮኖሚ ፍይዳ እንዲውል ማድረግ
3) ለሐረሪ ህዝብ አንድነት የሞት ሽረት ትግል ማድረግ አንድነት ሲባል የአስተሳሰብ አንድነት እንዲመጣ ጥረት በማድረግ የሐረሪን ህዝብ የልማት ተምሳሌት በማድረግ ክልላችንም እንደዚሁ እውነተኛ የፍቅር የመቻቻል የልማትና የቅርሶች ተምሳሌት ሆና መላውን ህዝብ ተጠቃሚ ማድረግ ::